ንፌስ የሕዝብ ዘብ ነው

# ጦቢያ

ጦቢያ፣ 6ኛ ዓመት ቁ. 6 ጥር 1991

## ኢትዮጵያና ኤርትራ ከእንግዲህ ወዴት? እንዴት?

መድረክ (ለመነጋገሪያ)

- «አሥመራ እንገናኝ»

ስንሻው ተገኝ


- ነባር እሴትና አዲስ አሳብ

ጸጋዬ ገ/መድኅን አርአያ

- የኤርትራ የዜግነት ቀውስና ምንጬ

ከባህታ



«ሕገ - መንግሥቱ በተጨባጭ የመድብለ ፓርቲን ሥርዓት አይፈቅድም»

ዶ/ር ነገደ ጎበዜ

- የልጅ ኢያሱ እስርና አሟሟት

(ከዓይን ምስክሮች)

# ቃለ - መጠይቅ

የዚህ ወር የቃለ መጠይቅ ዓምዳችን እንግዳ ዶ/ር ነገደ ጎበዜ ናቸው። በሁለተኛው የፓሪስ ጉባዔ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች (ኢተፖድኅ) ሊቀ መንበር ሲሆኑ ስለተቃዋሚ ድርጅቶች ኅብረት አስፈላጊነት፣ ስለ ትግሉ ጥንካሬና አቅጣጫ፣ በመጭው ምርጫ ተሳትፎ ላይ ስላላቸው አስተያየት አነጋግረናቸዋል። ዝርዝሩ ከዚህ በታች ሰፍሯል።



**ጦቢያ፦** ባለፈው መስከረም በፈረንሳይ ዋና ከተማ ፓሪስ ውስጥ ተደርጐ የነበረው የተቃዋሚዎች ስብሰባ ለምን አስፈለገ? ከመጀመሪያው የፓሪስ ስብሰባ በምን እንደሚለይ ቢገልጹልን፦

**ዶ/ር ነገደ ጎበዜ፦** የሃገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ኃይሎች አስተኛና ግልጽ የሆነ የጋራ ጥያቄ ይዘው በጋራ ይታገሉ፣ ሕዝቡ'ንም ያታግሉ የሚለው ጥያቄ የቆየ የሕዝቡና የጠቅላላው የኢትዮጵያ ታጋይ ኃይሎች ጥያቄ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ከመጀመሪያው የፓሪስ ጉባኤ ያገኘው ትምህርትም አለ። በጋራ ጥያቄዎች ዙሪያ ተቃዋሚዎች ሲታገሉ የሕዝቡ የትግል ወኔ ይቀሰቀሳል። ፀረ ዲሞክራቲክና ፀረ ሕዝብ ኃይሎች ወደ ተከላካይነት ይወርዳሉ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃም ይህ ነው የማይባል ድጋፍ ይገኛል። በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም የራሱን አማራጭ የሚለውን ነገር ይዞ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እስካለ ድረስ ፀረ ዲሞክራቲኩን ኃይል አንድ አቅጣጫ ይዞ መፋለም ይቀርና ተቃዋሚ ሁሉ «ከቦ የሚገፋበት» ሁኔታ ይፈጠራል። አንዱ ከቀኝ ወደ ግራ ሲገፋው ሌላው ከግራ ወደ ቀኝ ከገፉ አንዱ ከፊት ወደ ኋላ ሲገፉ ሌላው ከበስተኋላ ከገፋው ፀረ ዲሞክራቲኩ ኃይል ከመሃል ቀጥ ብሎ ይቀጥላል። በራሱ ቅራኔ፣ በራሱ ድክመቶች በደረመስ እንኳን የትላንት ተቃዋሚዎች እርስ በእርስ የሚባሉበት ሁኔታ ይፈጠር እንደሆን እንጂ ለሕብረተሰቡ የተረጋጋ የሰላምና የዲሞክራሲ ሁኔታ አይፈጠርም። ይህ የእስከዛሬው ትግላችን ያስተማረንና በቃን ያልነው ልምዳችን ነው።

ከዚህ ትምህርት በመነሳት ቢያንስ ቢያንስ ከሁለት ዓመታት ጀምሮ የቀድሞው የፓሪስ ጉባኤ አስተባባሪ ኮሚቴ አባሎች እንደገና ይህ ጥንስስ እንዴት ሊያነሰራራ እንደሚችል ብያዘ ለቀቅም ቢሆን ስንወያይ ቆይተናል። ነገር ግን የየድርጅቶቹ የየራሳቸው ውስጣዊ ሁኔታዎች፣ የትግል አቅጣጫና ትኩረት መሰበጣጠሮች ሰፍኖ ተቃዋሚ ኃይሎች ተሰባስበው እንደገና ወደ ፖለቲካና ዲፕሎማሲያዊ አጥቂነት እንዲሸጋገሩ በቀስተ ደመና ሬድዮ ካለፈው መስከረም 1990 ጀምረን ስንቀሰቅስ ቆይተናል። ከጥር ወር ጀምረን ይህንን ጥረት ከፍ አድርገን ነበር። በዚህ ሙከራ ላይ እያለን የሻዕቢያ እብሪተኛ ወረራ አዲስ የፖለቲካ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ምናልባት ሃገራችን ከዚህ ቀደም አጋጥሟት የማያውቅና ምናልባትም የወያኔ መሪዎች ገና ሙሉ በሙሉ ያልተከሰተላቸው የሕዝቦችን መጨራረስና የሃገርን ህልውና ከጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ አደገኛ ሁኔታ ፈጠረ። ቀደም ሲል ይታይ የነበረው የትግል መፍዘዝ አሁን ደግሞ አገርን ለማዳን በተቀሰቀሰ ስሜት በከፍተኛ የትግል እንቅስቃሴ ተተካ።

በተለይ ደግሞ የትግል አንድነት ጥሪ ከያለበት በመስተጋባቱ ሁሉም ከሁሉም ጋር በሁሉም ጥያቄ ላይ እየተስማማ መግለጫ የሚፈራረምበት አስደናቂ ወቅት ውስጥ ገባን። ይህ አዝማሚያ ለሃገር የሚበጅ ትክክለኛ የፖለቲካ አቅጣጫ እንዲይዝ የተቃዋሚ ኃይሎችን የጋራ ትግል ግልጽና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መድረክ ላይ መገንባቱ አስፈላጊ ሆኖ መጣ። በዚህ ሁኔታ የተለያዩ የብሄርና ህበረብሔር ድርጅቶች ተስማምተውባቸው የጸደቁትን የመጀመሪያውን የፓሪስና የአዲስ አበባ ጉባኤዎች አቋሞችና ሰነዶች እንደገና አድሶ ለወቅቱና ለመጪው ትግል የሃገሪቱን ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች በሙሉ ሊያስማማ የሚችል የጋራና ዲሞክራሲያዊ የሆነ የመታገያና የማታገያ ሰነድ ለመንደፍ ፓሪስ ሁለትን ከመጥራት የተሻለ አማራጭ አልነበረም።

ሁለተኛው የፓሪስ ጉባኤ የተጠራው ቀደም ሲል በአምስተርዳም ከተማ የቀድሞው የፓሪስ ጉባኤ አስተባባሪ ኮሚቴ ባደረገው ውሳኔ ነው። የአምስተርዳሙ ውሳኔ የመጀመሪያውን የፓሪስ ጉባኤ መሠረታዊ የፖለቲካ አቋሞች ሙሉ በሙሉ እንደገና አጽድቆ እነዚህን አቋሞች በተግባር ለመተርጐምና በጋራ ዲሞክራሲያዊ ሰነድ ላይ የጋራ ትግል የሚካሄድበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነበር። በመሆኑም ፓሪስ ሁለት የፓሪስ አንድ ቀጣይ ጉባኤ ሆኖ ሊታይ ይችላል። ሆኖም በሁለቱ መሃከል ልዩነቶች ይታዩኛል።

መጀመሪያ የበፊቱ የፓሪስ ጉባኤ አስተባባሪ ኮሚቴ ሲያቋቁም የዚህ ኮሚቴ ተግባሩም የተወሰነ የጊዜ ገደቡም እንደዚሁ የተወሰነ ነበር። ተግባሩ አገር አቀፍ የሰላምና እርቅ ጉባኤ ማዘጋጀት ነበር። ይህ ከተሳካ በኋላ የአስተባባሪው ኮሚቴ እንደገና ካልታደሰለት በስተቀር ተልእኮውም ህልውናውም አከተመ ማለት ነበር። ሁለተኛው የፓሪስ ጉባኤ የፈጠረው ኢተፖድህ ተግባሩ ዲሞክራሲ የሚጐለብትበትን፣ ለዲሞክራሲ የሚያመዝን የኃይል ሚዛን ተፈጥሮ ነፃ ምርጫ የሚደረግበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚደረገውን ትግል ማስተባበር ስለሆነ ተልእኮው ደብልጥ የፖለቲካ ይዘት አለው። ሁለተኛ ደግሞ የጊዜ ገደብ የለውም። በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ሰፍኖ ነፃ ምርጫ እስኪካሄድ ድረስ የሚቀጥል ስብስብ ነው።

ሁለተኛው ልዩነት የሚፈልቀው ከዚሠ ነው። የአሁኑ ጉባኤ ትኩረት በአመዛኙ የዲሞክራሲ ሂደትንና የነፃ ምርጫን የሚመለከት ስለሆነ ለኢትዮጵያ ታጋይ ኃይሎችና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን አገዛዝ ከእለት እለት ደብልጥ እየተደራጁ እንዲታገሉት የቀረበ ጥሪ ነው። በመሆኑም ከመጀመሪያው የፓሪስ ጉባኤ ይልቅ አሁን በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ታጋዮችን በድጋፍ ኮሚቴዎችም ሆነ በሌሎች ስብስቦች የማደራጀቱና የማንቀሳቀሱ ተግባር ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

**ጦቢያ፦** ሥልጣን ላይ ላለው መንግሥት ያስተላለፋችሁት ጥያቄ ምን ይመስላል? ምንስ ያህል ተቀባይነት አግኝታችኋል? ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ስለ ፓሪሱ ጉባኤ ተጠይቀው እንደሚቀበሉት ተናግረዋል። «ይምጡና እንፈታተሻለን» ያሉትን ምን ትርጉም ትሰጡታላችሁ?

ከመልሳቸው ብዙ ተስፋ አግኝታችኋል? ውይይትስ ጀምራችኋል?

**ዶ/ር ነገደ፡-** በፓሪሱ ጥሪ መሠረት የሃገራችንን ችግሮች በዲሞክራሲያዊ ዘዴ የምንፈታበትን ሁኔታ እንድንወያይ ደብዳቤ ጽፈናል። አያይዘንም የፓሪሱን ሰነዶች ልከንላቸዋል። መልስ አላገኘንም። ውይይትም አልጀመርንም። ይምጡ እንፈታተሻለን እሉ የተባለውን አልሰማሁም። ዲሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ ሁላችንም አቋማችንን ይዘን ኑና በሕዝብ ፊት እንፈታተሽ ማለት ከሆነ የጥሪያችን ይዘት ገብቷቸዋል ማለት ነው። የሚያወሩት ስለሌላ ዓይነት መፈታተሽ ከሆነ ግን አገራችንም፣ ራሳቸውም ከነድርጅታቸውና ከነአባሎቻቸው ያሉበት አደገኛ ሁኔታ አልገባቸውም ማለት ነው።

ከመልሳቸው ብዙ ተስፋ አግኝታችኋል ወይ ለተባለው ይህ የእናንተ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የብዙ ዜጎችን አእምሮ ያስጨነቀ ጥያቄ ሆኖ አግኝተነዋል። «ምን ይመልሱላቸው ይሆን? ወያኔ ውይይት አሻፈረኝ ቢል ምን ሊያደርጉ ነው?» የሚለው መጨነቅ በያለበት አጋጥሞናል። ነገሮችን ከዚህ አንጻር መቅረብ የኢትዮጵያችንን እድል ከሕዝቦቿና ከታጋይ ልጆቿ ትከሻ ይልቅ እጅግ አጠራጣሪ በሆነ በወያኔ መሪዎች ዲሞክራሲያዊነትና የሃገር ፍቅር ስሜት እንደማንጠልጠል ያህል አደገኛ አዝማሚያ ነው። የሚያመለክተው ነገር ቢኖር ስለ ፓሪሱ ጥሪ አንድ የሆነ አለመግባባት መኖሩን ነው።

እርግጥ የወያኔ መልስ አወንታዊ ወይም አሉታዊ መሆኑ በአጭር ጊዜ ሲታይ ለመጪው ትግላችን፣ ለሃገራችን ሰላምና ለሕዝቦቿ ወንድማማችነትና አንድነት አዎንታዊም አሉታዊም ተጽዕኖ ሊኖረው ስለሚችል አንጨነቅበትም ማለት አይደለም። በወያኔ ውስጥ ለጊዜው ማኖል ያልቻሉት ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች ይበልጥ አይለውና አሸንፈው በሃገራችን ትርጉም ያለው ብሔራዊ ውይይት ከተካሄደ ለሀገራችን በእርግጥም አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ይከፈታል። የሥልጣን ጥመኞችና የሻዕቢያ ሠርጐ ገቦች ከአየሉና ልክ እነኢሳይያስ አፈወርቂ እንደሚመኙት ችግሮቻችንን በውይይትና በዲሞክራሲ ቀድመን እንዳንፈታ ከተደረግን መጭው ጊዜ ለኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን እንደሚሆን በበኩሌ ምንም ጥርጥር የለኝም።

የሆነ ሆኖ ለእኛ ወሳኙ ጥያቄ የወያኔ መሪዎች መልስም መልካም ፈቃድም አይደለም። የፓሪሱ ጥሪ በመሠረቱ የኢትዮጵያ ሕዝብና የሃገራችን ታጋይ ኃይሎች ተሰባስበውና ተደራጅተው ለዲሞክራሲና ለሃገር ህልውና ሲሉ ወያኔ/ኢህአዴግን እንዲታገሉት የቀረበ ነው። ስለሆነም የእኛ ዋና ጭንቀት የዚህ ጥሪ ዋና ባለጉዳይ የሆኑት ወገኖቻችን ምን መልስ ይሰጡ ይሆን የሚል ጭንቀት ነው። ጥሪያችንን ሰምተው ለፓሪሱ ዓላማዎች ተግባራዊነት ከተደራጁና ከተንቀሳቀሱ ወያኔ ተወያየ አልተወያየ ይዋል ይደር እንጂ በሃገራችን ዲሞክራሲ ይሰፍናል።

በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ጥሪ ዙሪያ ታጋይ ኃይሎች እስካልተንቀሳቀሱ ድረስ ወያኔ ከአንገት በላይ ጥሪውን ቢቀበል እንኳን በተለያዩ አሻጥሮች፣ የውስጡንና የውጭን ተቃዋሚ ኃይል በመከፋፈል፣ በሌሎችም ዘዴዎች በመጠቀም ትርጉም ያለው ብሔራዊ ውይይት እንዳይካሄድ ማከላከሉ የማይቀር ነው። የተደራጀ የሕዝብ ግፊት በሌለበት ሁኔታ ብሔራዊ ውይይት ይካሄዳል ብሎ ማሰብ፣ ቢካሄድም ፍሬያማ ይሆናል ብሎ መገመት የወያኔ መሪዎች በልመና ማመልከቻ ልባቸው ይራራል፣ ራሳቸውን በራሳቸው አርመው የሃገር ፍቅርና የኃላፊነት ስሜት ይላበሳሉ ብሎ እንደመጠበቅ ይቆጠራል። በበኩሌ ይህ የማይመስል ነገር ነው እላለሁ።

**ጦቢያ፡-** ቀደም ሲል ከነበራችሁ መሠረታዊ አቋም ብዙውን ወደ ጐን ትታችሁ ወይም መርሆዎችሁን ለውጣችሁ የቀረባችሁ ይመስላል። ከጥንካሬ አንጻር የቀረባችሁ ናችሁ ወይስ ከመድከምና እጅ ከመስጠት?

**ዶ/ር ነገደ፡-** ምንም የተቀየረ አቋም የለም። ከፍ ብዬ እንዳልኩት ፓሪስ ሁለት የተጠራው በቅድሚያ በመጀመሪያው የፓሪስ ጉባኤ የጸደቁትን መሠረታዊ የፖለቲካ አቋሞችና መርሆዎች አንዳንዱም ቃል በቃል አድሶ በተቀበለው የአምስተርዳሙ ስብሰባ ነው። በፓሪሱ የመጀመሪያ ስብሰባ ስለዲሞክራሲያዊ ሂደት፣ ስለነጻ ምርጫና ስለዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት የተወሰዱት አቋሞች ዘርዝር ባለ ሁኔታ ቀርበው የጋራ ትግል ሠነድ እንዲወጣቸው በተጠየቀው መሠረት ነው ሁለተኛው የፓሪስ ጉባኤ የሠራው። በዚህ ጉባዔ ላይ የጸደቀው «የዲሞክራሲ ሂደትና የነጻ ምርጫ ትልም» የተሰኘው ሰነድ ደግሞ ራሱም ቢሆን ከአራት ዓመት በፊት በኢዴሃቅ አመራር ጸድቆ በአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ተቀባይነት ካገኘው «ለአዲስ ዲሞክራሲያዊ ጅማሮ» ከሚለው ሰነድ ብዙም የሚለይ አይደለም። ባጭሩ ነበር እንጂ የተቀየረ አቋም የለንም።

ለየት ያለ የሚመስል ነገር ሲኖር ለብሔራዊ ውይይት የተደረገው ጥሪ ነው። ይህም ምንም አዲስ ነገር የለውም። የመጀመሪያው የፓሪስ ጉባኤ ሲደረግ ኢህአዴግም እንዲገኝና በውይይቱ እንዲካፈል ጥሪት ተደርጐ ነበር። ለአዲስ አበባውም ጉባኤ «አገር አቀፍ የሰላምና እርቅ ጉባኤ» እስከተባለ ድረስ የኢህአዴግም መገኘት ትርጉምና አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ ስለታመነበት እንዲገኙ ጥሪት ተደርጐ ነበር። እንዳሁኑ ደብዳቤ ተጽፎላቸው አልመለሱም። ይህም የተጠበቀ ነገር ስለነበረ እነሱ ቀሩ ብለን የጉባኤውን ነገር አልተውነውም።

በአሁኑ ጉባኤ እርግጥ ይህ የብሔራዊ ውይይት ጥሪ ጉላ እንዲል ተደርጓል። ይህ ጥሪ፣ ከድክመት፣ የመነጨ ጥሪ የሚመስላቸው ሰዎች ካሉ ትልቅ ስሁተት ነው።

አንደኛ ነገር እንወያይ የሚለው ጥሪ የድክመት ምልክት ይሆን የነበረው «አይ ወያኔ በትግል አልተቻለም እስቲ ደግሞ በማግባባትና በመለማመጥ እንሞክር» ብለንና «ትግል ሰልችቶናል ውይይት እንሞክር» ብለን ብንነሳ ነበር። ጥሪያችን የድክመት ምልክት ይሆን የነበረው ውይይትን የትግል ምትክ አድርገን ብንወስደው ነበር። ከፍ ብዬ ላስረዳ እንደሞከርኩት የውይይቱ ጥሪ መንፈስ ጨርሶ ይህ አይደለም። ሺህ ጊዜ ቢደጋገም የሚበቃ አይመስለኝም። የፓሪሱ ጥሪ ዋና ዝጋታው ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዚች አገር ዲሞክራቶች ወያኔና በይበልጥ ተደራጅተውና ተጋግዘው እንዲታገሉት የቀረበ የትግል ትግግዝ ጥሪ ነው።

ሁለተኛውና ዋናው ነገር ደግሞ ዛሬ ሃገራችን በሻዕቢያ ወረራ ምክንያት ባለችበት አደገኛ ሁኔታ ይህ የውይይት ጥሪ የድክመት ሳይሆን የብስለትና የኃላፊነት ስሜት መላበሳችን ምልክት ነው እላለሁ። ስለዚህ ብሔራዊ ውይይት ምንነትና አስፈላጊነት በዛው በፓሪሱ ጉባኤ በጸደቀው ሰነድ ላይ በሰፊው ተዘርዝሯል። የውይይቱ ጥሪ የተቃዋሚ ኃይሎችን ብስለትና የኃላፊነት ስሜት ያንጸባርቃል የምልበት ምክንያት ዛሬ ሃገራችን ባለችበት አስቸጋሪ ሁኔታና በሻዕቢያ ሴራ ምክንያት ከሚጠብቃት አደጋ አንጻር ሲታይ ይህ ጥሪ የፀረ ሻዕቢያው ትግል የማይነጠል አካል መሆኑ ነው። ሻዕቢያና ሠርጐ ገቦች የሃገራችን ችግሮች በሰላም ሳይሆን በትርምስ፣ በዴሞክራሲ ሳይሆን በመተላለቅ ሊፈቱ የሚችሉ በማስመሰል የኢትዮጵያን ህልውና ክፉኛ በመፈታተን ላይ ናቸው። በመሆኑም ዲሞክራሲና ብሔራዊ ውይይት ስንል ዶሮ ብታልም ያን ጥሬዋን እንዲሉ አንዳንድ የወያኔ መሪዎች የሥልጣን ሽሚያ መሰላቸው እንጂ በእኛ በኩል ይህ ጥሪያችን የነሻዕቢያን ሤራ ከማክሸፍ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይገባም።

**ጦቢያ፡-** አቶ አረጋዊ በርሄ ቀድሞ የወያኔ መሪ መሆናቸው ይታወቃል። እርስዎ የመኢሶን መሪ ሆነው ቆይተዋል። የድርጅቶቻችሁ ባለት (ኮንስቲቱኤንሲ) የት ነው? ምንድን ነው?

**ዶ/ር ነገደ፡-** ከአቶ አረጋዊ ጋር ከመጀመሪያው የፓሪስ ጉባኤ ጀምረን ነው የምንተዋወቀው። ለሁለተኛው ጉባኤ ዝግጅትም ከጥንስሱ ጀምረን አብረን ሠርተናል። ለዚህ ጉባኤ መሳካትም ብዙ የደከመ ሰው ነው። ኢትዮጵያዊ የሆነ ራእይ ያለው ታጋይ መሆኑንም ለመገንዘብ ችያለሁ። ሌሎቹን ጥያቄዎች እሱ ራሱ ቢመልስ የሚሻል ይመስለኛል።

መኢሶንን በተመለከተ እንደማገኘውም በመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ውስጥ ለመታገል እንደሚፈልግ የፖለቲካ ድርጅት የመንቀሳቀሻ አካባቢው (Constituency) መስፋት ወይም መጥበብ የሚወሰነው ባለው የፖለቲካ ፕሮግራም፣ ይህንን ፕሮግራም አንግቦ ለመታገል በሚያሳየው ታታሪነትና በሕብረተሰቡ ውስጥ «ይህ ድርጅት የኔ ነው» ብሎ ሊያቅፈው የሚፈልገው የሕብረተሰብ ክፍል መብዛቱ ወይም ማነሱ እየታየ ነው። ዲሞክራሲና

ነጻ ምርጫ በሌለበት ሁኔታ ይህ ኮንስቲቱሴንሲ ምን ያህል ስፋት እንዳለው መናገር አይቻልም። የሆነ ሆኖ መኢሶን ዛሬም እንደትላንቱ በእኩልነትና በወንድማማችነት ላይ ለሚገነባ የኢትዮጵያ አንድነት፣ ከማህበራዊ ፍትህ በምንም ዓይነት ለይቶ ለማያየው የኢኮኖሚ ልማትና እድገት፣ ትርጉምና ክብር ካለው ሕልውና ነፃሉ ለማያየው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ነጻነትና ሉአላዊነት ይታገላል። ይህንንም ራእይ በተግባር ለመተርጎም እንደማኛውም ድርጅት የራሱ የአደረጃጀት ስልት፣ የራሱ ስትራቴጂና የራሱ ቅደም ተከተሎች አሉት።

ዛሬ ባለንበት ወቅት የዚህ ቅደም ተከተል ዋና ገጽታ ማንም አገር ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያዊ ሊኖረው ይገባል ከምንለው ቅደም ተከተል ወይም ትኩረት የተለየ ሊሆን አይችልም። የባሻገሩን ለቀቅ አርጐ የሸማግሩን ጥያቄ አጥብቆ መያዝና ለዲሞክራሲ መደረግ ባለበት የጋራ ትግል ላይ መረባረብ ያስፈልጋል። የኛ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት (ኢተፖድኅ) ውስጥ የተካተቱትና ከዚያም ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን የሚታገሉት በዚህች አገር ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲገነባና ሥር እንዲሰድ ነው። ዛሬ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙ የመኢሶን አባላትና ደጋፊዎች የሚደክሙት ይህንን የጋራ ትግል ፈር ለማስያዝ በሚደረገው የኢትዮጵያውያን ጥረት የቻሉትን አስተዋጽኦ ሁሉ ለማድረግ ነው። ለጋራ ዓላማ የጋራ ትግልን ስትራቴጂ ማስቀደም መሥራትን በተለይ ከመጀመሪያው የፓሪስ ጉባኤ አንስተን ያመንበት፣ እንደ አበራ የማነ አብ የመሰለ መሪያችንን ከትግል ሜዳ ማራቅን ያህል ከባድ መስዋእትነት የከፈልንበት ዓላማ ነው። በሃገራችን የዲሞክራሲው ሂደት ዳብሮ ለነጻ ምርጫ አመቺ የሆነ የኃይል ሚዛን እስኪመቻች ድረስ ለዚህ የጋራ ዓላማ ቅድሚያና ትኩረት እየሰጠን ትግላችንን እንቀጥላለን።

**ጦቢያ፦** ከመጀመሪያው የፓሪስ ስብሰባ በኋላ የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ተቋቁሟል። የሁላችሁንም አቋም ምክር ቤቱ ይወክላል? ከሆነ ለምን ሁለተኛው የፓሪስ ጉባኤ ተጠራ? አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤትስ ለምን ተዳከመ?

**ዶ/ር ነገደ፦** የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት የተቋቋመው አብዛኞቹ የፓሪስ ጉባኤ ጠንሳሽ ድርጅቶች ባልተሳተፉበት ጉባኤ ቢሆንም ከራሱ «አማራጭ ኃይሎች» ከሚለው ስም አንስቶ እስከተቋቋመበት መሠረታዊ ሠነድ ድረስ የፓሪሱ አስተባባሪ ኮሚቴ ባቀረበው የመንደርደሪያ መሠረት የተዋቀረ ስብስብ ነው። ይህ ስብስብ የተለያዩ ዴሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ኃይሎች በኢኮኖሚ፣ በሶሻልና በተለያዩ የህብረተሰቡ ጥያቄዎች ላይ የተለያዩ ፕሮግራማቸውን እንደያዙ ሆነው በጋራ በሚስማሙባቸው ጥያቄዎች ላይ ትግላቸውን ማስተባበር እንዲችሉ ታስቦ የተጠነሰሰ መድረክ ነበር። እነዚህ የጋራ ትግላችን መድረክ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡት ነጥቦች የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ፣ የብሔር/ ብሔረሰቦች መብትና የኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት ጉዳይ፣ የነጻ ምርጫና የዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ጥያቄ ነበሩ። ቡተሰበጣጠሩ ምክንያቶች በነዚህ የጋራ አቋሞች ላይ የጋራ ትግል ለማድረግ የውስጡንና የአገር ውጩን ተቃዋሚ ኃይል ለማስተባበር የተደረገው ጥረት ሳይሳካ ቀረ።

በመሃል አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት እነዚህን አነስተኛና የጋራ የሆኑ ዲሞክራሲያዊ አቋሞች እንደያዘም ቢሆን ከነዚህ በተጨማሪ በማህበራዊና በኢኮኖሚ እንዲሁም በሌሎች ጥያቄዎች ላይ የራሱ ፕሮግራምና ራእይ ያለው ግንባር ሆኖ በህጋዊነት ተመዘገበ። ይህ የፓርቲ ፕሮግራሙ ብዙ ዜጎችን ሊያሰባስብለት እንደሚችል መጠራጠር አይቻልም። ነገር ግን እዚያው በዚያው ደግሞ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎችን በሙሉ የማሰባሰብ እድሉ አከተመ።

ሌላውን ሁሉ ትተን ለምሳሌ በሀገራችን ወሳኝ የሆነውን የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ ብንወስድ የምናየው ነገር አለ። ፓሪስ አንድ በእዚህ ላይ አቋም አልወሰደም። ተሳታፊ ድርጅቶች በዚህ ጥያቄ ላይ ተመሳሳይ አቋም ስላልነበራቸው ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚ ድርጅቶች የትግል ትብብር ዓላማ ሁኔታዎችን ለነጻ ምርጫ ማመቻቸትና ከነፕሮግራማቸው ሕዝብ ፊት መቅረብ በመሆኑ ነው። አሁን አማራጭ ኃይሎች መሬት የግል ሀብት መሆን አለበት የሚል አቋም ወይም ፕሮግራም ይዞ ወጣ። በዚህ ጥያቄ ላይ የተለየ አቋም ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች /ለምሳሌ እንደ ኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ/ በአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ፕሮግራም ሊወከሉ አይችሉም ማለት ነው።

ባጭሩ አሁን ባለው ሁኔታ አማራጭ ኃይሎች በሃገሪቱ እንደ አንድ ዋና ተቃዋሚ ኃይል ሊወሰድ ይችላል እንጂ ተቃዋሚዎችን በሙሉ የሚያሰባስብና የሚወክል ድርጅት ሆኖ ሊወሰድ አይችልም። እንዲያውም ሁለተኛው የፓሪስ ጉባኤ ያስፈለገበት አንዱ ምክንያት ዝቅተኛና ሁሉን ሊያስማማና ሊያካትት የሚችል የጋራ ሰነድ ነድፎ በዚህ አነስተኛ የጋራ አቋም ላይ ብቻ የጋራ ትግል የሚፋፋምበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው።

አማራጭ ኃይሎች ለምን ተዳከመ ለተባለው መቸም ድክመቱን በዚህ ድርጅት ላይ ብቻ መጣል ትክክል አይሆንም። የሁላችንም ድክመት ነው። ለዚህ ድክመታችን ተጠያቂ ማነው የሚለው ጥያቄ ደግሞ የወያኔ አፋኝ አገዛዝ ነው በሚል መልስ ብቻ ሊሸኝ የሚችል አይመስለኝም። ለዲሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ምን ግፈኛና አፋኝ አገዛዝ ቢሆን ፀረ ዲሞክራቱ አገዛዝ አገደብን፣ አፈነብን ብለን ይህንን እንደዋና ምክንያት ካቀረብን የማንወጣው አዙሪት ውስጥ እንገባለን። የፀረ ዲሞክራቲክ አገዛዝ መስፈን ብቻውን ለዲሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ዘላቂነት ባለው ሁኔታ የትም መቼም ሊገታና ሊያከሽፍ አይችልም። ይህ ቢሆን ኖሮ በደቡብ አፍሪካ ዘረኛው አገዛዝ ባልፈራረሰ ነበር። ይህ ቢሆን ኖሮ ዛሬ በደርዘን የሚቆጠሩ የአፍሪካ አገሮች ለዲሞክራሲና ለመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ባልበቁ ነበር። ይህ ቢሆን ኖሮ ኢንዶኔዥያን ለሰላሳ ዓመት አንቀጥቅጦ የገዛው የጄኔራል ሱሃርቶ መንግሥት በተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፎችና በሕዝብ ግፊት ተፍረክርኮ ባልወደቀ ነበር።

ዋናው ጥያቄ የሥርዓቱ አፋኝነት ሳይሆን በዚህ አፈናና ጭቆና ለተንገፈገፈውና ለመታገል ለሚፈልገው ሕዝብ፣ ለሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ተስማሚ የሆነ የትግል ስልትና ታክቲክ እያወጡ ትግሉ ከእለት እለት እያየለና አገዛዙን እያስጨነቀ፣ እየከፋፈለና እያዳከመ የሚሄድ «ብጉ አዙሪት» ውስጥ የመግባት ጥያቄ ነው። እስካሁን እንዲህ ዓይነቱ «ብጉ አዙሪት» ውስጥ እንዳንገባ ያደረጉን ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከነዚህ ውስጥ ከመጀመሪያው የፓሪስ ጉባኤ በኋላ ለጋራ ድክመታችን ምክንያት የሆኑትንና አሁን ደግሞ እንዳይደገሙ ልንጠነቀቅባቸው የሚገቡንን አንድ ሁለት ነጥቦች ማንሳት እወዳለሁ።

የመጀመሪያው ነጥብ በተቃዋሚ ኃይሎች ሰፈር በጋራ አቋም ላይ በጋራ ለመቆም ያየነው ጽናት አነስተኛ መሆኑ ነው። ከመጀመሪያው የፓሪስ ጉባኤና ከአዲስ አበባው ጉባኤ በኋላ በተነደፉት ሰነዶች አማካኝነት ያኔ የነበረውን ሕብረትና የጋራ ትግል መንፈስ ሁላችንም መንከባከብ ነበረብን። በውስጥና በውጭ ያለነው ተቃዋሚዎች በየትግሉ ምዕራፍ የሚከሰቱትን ችግሮች በጋራ እየመረመርን በጋራ ለማሸነፍና የሕዝቦችንን የጸኑት ቀን ለማፋጠን የሚያስችሉንን መዋቅሮችና መድረኮች እያመቻቸን ህብረታችንን ማዳበር ነበረብን። ከዚህ ይልቅ ከአዲስ አበባው ጉባኤ ማግሥት አንስቶ ከሞላ ጐደል ሁሉም መልሶ የራሱን የብቻ ትግልና አማራጭ ጉዳና፣ የራሱን የትግል ስትራቴጂና ቅደም ተከተል የሚያራምድበት ምዕራፍ ውስጥ ገባን። በዚህ ላይ የወያኔ መሪዎችና አንዳንድ ባዕዳን የውጪውን ተቃውሞ ኃይል በሃገር ውስጥ ካለው ተቃዋሚ ኃይል ለመከፋፈል ያደረጉት ጥረት ሲጨመር የሕብረት ትግላችን ደብዛው የጠፋበት ሁኔታ ተፈጠረ። ፓሪስ ሁለት የተጠራው ይህንን ሁኔታ አርሞ እንደገና የትግል ህብረታችንን ግልጽና ቀላል በሆኑ ዲሞክራሲያዊ ዓላማዎች ላይ ለመመስረት ነው። ይህ ጥረታችን እንደገና ታጥቦ ጭቃ እንዳይሆን ራሳችን የፈጸምናቸውን ስህተቶች እንዳንደግም መጠንቀቅ ይኖርብናል። በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች የሚቃጡብንን የመከፋፈል ሙከራ ንቅተን መጠበቅና ማክሸፍ ይጠበቅብናል።

በአንዳንድ አካባቢዎች የምንሰማው አሁንም የሃገር ውስጡን ተቃዋሚ ኃይሎች ውጭ ካለው ተቃዋሚ ኃይል ለመክፈል ሙከራዎች ተጀምረዋል። ይህ መጠበቅ ያለበት ክስተት ነው። በእኔ ግምት

የዲሞክራሲያው ሂደት ይጐልብት፣ ነጻ ምርጫ ይካሄድ፣ የሃገራችን ችግሮች በብሔራዊ ውይይት ይፈቱ ብለን ያቀረብነውን ጥሪ ወያኔ አፍ አውጥቶ ሊቃወመው አይችልም። የሚሞክረው በተለመደ ሢረኛ አሠራሩ ማክሸፍ ወይም ትርጉም ማሳጣት ነው። ዋናው ጥያቄ ለዚህ በምንም ዓይነት በአክራሪነት ሊፈረጅ ለማይችል ሃገራዊና ዲሞክራሲያዊ ጥሪ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ መልስ የመስጠት ጥያቄ ሆኖ ሳለ ወያኔና ደጋፊዎቹ ተቃዋሚዎቻቸውን ራሳቸው ለመምረጥና ለመመልመል የሚሞክሩበት ሁኔታ ይታያል።

በዲሞክራሲያዊነቱ የማያወላዳና በብሔራዊ ኃላፊነት ስሜቱ ምንም የማይወጣለት የጋራ አቋም ይዘው የሚታገሉ ኃይሎችን ለመከፋፈል የሚያደርጉት ሙከራ «እንደምንም እናግባባቸዋለን» ብለው ከንቱ ተስፋ የጣሉባቸውን ተቃዋሚዎች በዚህ የጋራ ሰነድ ተመርኩዘው እስከመጨረሻው ይፋለሙናል ብለው ከሚፈሯቸው ተቃዋሚዎች ለመነጠል እንደሆነ ግልጽ ነው። ካለፈው ልምዳችን ሁላችንም ብዙ ትምህርት ቀስመናልና እዚህ ወጥመዳቸው ውስጥ የሚገባና ፓሪስ ሁለት እንደገና ለሕዝባችን የፈነጠቀውን የተስፋ ጭላንጭል መልሶ የማውደም ኃላፊነት የሚቀበል ያለ አይመስለኝም።

ሁለተኛው የድክመታችን ምክንያት የተቃዋሚ ድርጅቶች ትግል ከዋናው ባለጉዳይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የእለት ተእለት የመብትና የሕልውና ችግሮቹ ይህ ሕዝብ በግብታዊነት በማካሄድ ላይ ካለው ትግል ለማዋሃድ አለመቻላችን ይመስለኛል።

የኢትዮጵያ ችግሮች መሠረታዊ ምንጫቸው ወያኔ የተከለው ግፈኛና ኢፍትሃዊ አገዛዝ ነው። ይህ አገዛዝ በሕብረተሰቡ ውስጥ ከአሸዋ የበዙ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ ኑሮና ፍትህ ችግሮች እንዲፈሉና እንዲባባሱ ያደረገ አመራር ነው። ዋናው ችግርና የመፍትሔው ቁልፍ ፖለቲካ ቢሆንም የትግል መስክ እንደችግሮቹ የተሰቦጣጠረና ከአሸዋ የበዛ ነው። ከዚህ መሠረታዊ ሃቅ ካልተነሳን በአንድ በኩል ያለው አደጋ ትግላችንን በፖለቲካዊ ጥያቄዎች ላይ ብቻ የሚያተኩር፣ በፖለቲካ የነቃውን ክፍል ከማንቀሳቀስ የማያልፍ የጥቂቶች ትግል የማድረጉ አደጋ ነው። ሌላም ቁም ነገር አለ። ዛሬ በሃገራችን እንደኛ የሰው ልጅ መብት፣ ነጻ ምርጫ፣ ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት አይበሉ እንጂ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጐች የወያኔ አገዛዝ በኑሯቸው፣ በመብታቸው በህልውናቸው ስለመጣባቸውና ሌላ ምንም ምርጫ ስላልሰጣቸው የእለት ተእለት ትንቅንቅ ላይ ይገኛሉ። ይህ በየእለቱ በዓይናችን ሥር በግብታዊነትና በአልሞት ባይ ተጋዳይነት እየፈነቀለ የሚወጣውና ሰብሳቢም ሆነ አመራር ያጣ ትንቅንቅ ነው። ዛሬ ሃገራችን ባለችበት ሁኔታ ይህ የሚሊዮኖች ግብታዊ ትንቅንቅ አማራጭ አቅጣጫ እያሳየና እያስተባበረ የሚመራው የፖለቲካ ኃይል ካላገኘ ኢትዮጵያ ለአክራሪዎችና ለደመኛ ጠላቶቿ ብቻ የሚያመቹ ፍንዳታዎችና ውስብስብ ችግሮች እንዳያጋጥሟት እሰጋለሁ፡

በየአምስት ዓመቱ ከሚደረጉ ምርጫዎች አንጻር ነጻ ምርጫ፣ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ለሚለው ስትራቴጂያዊ ዓላማ መቆምና መታገል ደግሞ ብቻውን ይህንን አደኛ ክፍተት አይዘጋውም። ለዲሞክራሲ የሚያደላ የኃይል ሚዛን ለመፍጠር የግድ አስፈላጊ የሆነውን ህዝባዊ የእለት ተእለት ትግልም አይተካውም። የቅድመ አብዮት ዘመኑን ትግል ዘወር ብለን ብንመለከት «መሬት ለአራሹ» የተባለው ስትራቴጂያዊ መፈክር ከተነሳ በኋላ ለአስር ዓመታት ያህል አገዛዙን ማዋከብ፣ ማዳከምና መከፋፈል የተቻለው ነጋ ጠባ «መሬት ላራሹ» በሚል መፈክር ስር ሰልፍ በመውጣት አልነበረም። ትግሉ ከዓመት ዓመት እየሰፋና እየተፋፋመ የሄደው ከዚህ መፈክር ጋር ቀጥታ ግንኙነታቸው በማይታይ የተሰቦጣጠሩ ጥያቄዎች ዙሪያ እየተንቀሳቀሱ ፊውዳሉን መንግሥት በመጋፈጥ ነበር።

አሁንም ከዚህ ሌላ አይታየኝም። በፖለቲካ እምነትና ራእያቸው፣ በሃገር ፍቅር ስሜታቸው ተገፋፍተው ለመታገልና ለመሰዋት የተደራጁት በሺህ የሚቆጠሩ ዜጐች የወያኔ አገዛዝ አንገፍግፏቸው በግብታዊነት ለመብታቸውና ለህልውናቸው በመታገል ላይ ካሉት ሚሊዮኖች ጋር ትግላቸውን ካላቀናጁ የሃገራችን ነገር ፍየል በዚህ ቅዝምዝም በዚያ ሆኖ ሲቀጥል ይታየኛል።

**ጦቢያ:-** ስለሚመጣው ብሔራዊ ምርጫ ያለዎት አስተሳሰብ ምንድን ነው? እናንተስ ምን ያህል ተዘጋጅታችኋል?

**ዶ/ር ነገደ:-** ከፍ ብዬ እንዳልኩት ለውይይቱ ጥሪ መንግሥት ምን መልስ ሰጠ የሚለውን ጥያቄ በሁለተኛ ደረጃ እንደምናየው ሁሉ ይህንን የ1992 ዓ.ም ምርጫም እንደ ትግላችን አልፋና ኦሜጋ አርጐ መቁጠር ስህተት ነው እላለሁ። የኢተፖድህ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ እንዲሰፍን መታገል ነው። በዚህ አማካኝነት ወደ ነጻ ምርጫና ወደ መድብለ ፓርቲ ሥርዓት ለመሸጋገር በጋራ ለመታገል ተነስተናል። ለዚህ መሳካት ደግሞ ከእለት እለት በደብልጥ እየተደራጀንና የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ዲሞክራሲያዊ አማራጭ የራሱ አማራጭ አርጐ እንዲወስደውና ከእለት እለት በደብልጥ እየተደራጀ እንዲታገል ጥረት እናደርጋለን። ምርጫ የሚሉ ነገር በእርግጥም ነጻና ርትአዊ ሊሆን የሚችለው የዚህ የዲሞክራሲ ሂደት ውጤት ሲሆን ብቻ ነው። ነጻ ምርጫ የፀረ ዲሞክራሲ ሥርዓት የቀብር ሥነ ሥርዓት እንጂ የዲሞክራሲ ሥርዓት አዋላጅ ኃይል ሊሆን አይችልም። የትም ሆነ ምንጊዜም እንደዚህ ዓይነት የቅደም ተከተል መምታታት ሲኖር ለዲሞክራሲ የበጀ ነገር ፈልቆ አያውቅም። ቅደም ተከተሉም ተምታቶ ሲቀርብ የሚያግዘው ፀረ ዲሞክራሲውን ሥርዓት ብቻ ነው።

ዲሞክራሲ በቅድሚያ ባልሰፈነባቸው ህብረተሰቦች ሁሉ የሚደረጉ ምርጫዎች ራሱ አገዛዙ ሳይቀር ህብረተሰቡን አፍኖ ለመያዝ ከሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች መሃል እንኳን እንደ እንጀራ ልጅ በሁለተኛ ደረጃ የሚያያቸውና የሚንቃቸው ሂደቶች ናቸው። ከአገዛዙ መሣሪያዎች ለምሳሌ ሠራዊት ከድቶ መንግሥት ሊገለብጥ ይችላል። በፀረ ዲሞክራቲክ መንግሥት የተቋቋመ የምርጫ ቦርድ ከድቶ ያልተጠበቀ ውጤት ያመጣበትና መንግሥት የተቀየረበት ሁኔታ ግን ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም። ከዚህ የተነሳ ነው ደግሞ መንግሥት የሚንቃቸውን ያህል ሕዝቡ ደግሞ ከመጤፍ የማይቆጥራቸው።

ያለ ዲሞክራሲ የሚካሄዱ ምርጫዎች ፋይዳ ቢስ ናቸው ስለተባለ ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች አደገኛ አይሆኑም ማለት አይደለም። አፋኙ መንግሥት ለውጥን ለማዘግየት፣ የተቃዋሚዎችን ሰፈር ለመከፋፈል፣ ሕዝቡን ግራ ለማጋባት ይጠቀምባቸዋል። የሃገራችን ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች እንዲህ ዓይነቱ ወጥመድ ውስጥ ዘው ብለው እንዳይገቡ በጣም መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል። በዲሞክራሲ ሂደትና በነጻ ምርጫ መሃከል ስላለው ግንኙነት ግልጽና የማያሻማ የጋራ አቋም መያዝ ይኖርባቸዋል። የፓሪስ ሁለት አንዱና ዋናው ድል ይህንን ዓይነቱን የጋራ አቋም ማስያዙ ስለሆነ በሱ ጸንቶ መቀጠል የወያኔን የመከፋፈል ሴራ ለማክሸፍ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው።

የጋራ ትግላችንና ትኩረታችን መጭው ምርጫ ሳይሆን የዲሞክራሲው ትግል ሥር መስደድ መሆን ይኖርበታል። ካሁኑ ዲሞክራሲው ትግል ላይ ካተኮርንና ሕዝባችንን ለዚህ ትግል በሕብረት ለማንቀሳቀስ ከቻልን የመጣ ቢመጣ ትግላችን ከእለት እለት እየሰፋና እየዳበረ የሚሄድበትን ሁኔታ እያመቻቸን ሄድን ማለት ነው። የኛ ትኩረት መጪው ምርጫ ላይ ሆኖ የሕዝባችንም ትኩረት እዛ ላይ ብቻ እንዲሆን ካደረግን ግን ከ1992 ዓ.ም በኋላ ደግሞ እስከሚቀጥለው ምርጫ ድረስ የምንለው ያጣን እንዳይመስልብን እሰጋለሁ።

በዚህ ፀረ ሕዝብ ሥርዓት ሥር በሕብረተሰባችን ፊት ከአሸዋ የበዙ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ የእለት ተእለት ሕልውና ጉዳዮች አፍጥጠውና እንደዚሁ ከአሸዋ የበዙ የወያኔን መታገያ መስኮች እያሉ እነዚህን ችላ ብሎ ምርጫ ላይ ብቻ ማተኮር ትግላችንን በየአምስት ዓመቱ ቀን ቀጠሮ ይዞ የሚያገረሽ የምርጫ ሰሞን ግርግር እንዳያስመስልብን መጠንቀቅ ይኖርብናል።

ይህ ሁሉ ስለተባለ የዛሬ ዓመት ተኩል ይደረጋል የተባለውን ምርጫ እንደሌለ ነገር እንቁጠረው ማለት አይደለም። ወያኔ በበኩሉ

ወደ ገጽ 22